## የስሜት አካላት

በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቃላት እየመረጣችሁ ክፍት ቦታው ላይ አስገቡ።

|  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|
| ማየት | መቅመስ | መስማት | መዳሰስ | ማሽተት |

በሬዲዮ ስለሎሚ ጥቅም ሲነገር ________ ቻልኩ። ሰምቼ ለእናቴ "ሎሚ ግዢልኝ" አልኩ። "ተገዝቷል፣ ቦርሳው ውስጥ ፈልገው" አለችኝ። የእናቴን ቦርሳ ________ ደስ ይለኛል። በጣም ይለሰልሳል። ቦርሳውን እየዳሰስኩ ወደውስጥ ________ ስሞክር፣ ትንሽ ሎሚ አየሁ። አነሳሁት። ለእናቴ "አፍንጫዬን ሳላስጠጋ________እችላለሁ?" ብዬ ጠየቅኳት። "አፍንጫህ ላይ ብዙ ሳታስጠጋ አሽትተው" አለችኝ። ሳሽተው ደስ አለኝ። "ቆርጠሽ ስጭኝና ልምጠጠው" አልኳት። ቆርጣ ሰጠችኝ። ከመምጠጤ በፊት በምላሴ________ ፈለግኩ። ቀመስኩት። በጣም ጎመዘዘኝ።


© www.keenworksheets.com

## የስሜት አካላት

በሰንጠረዡ ውስጥ ያሉትን ቃላት እየመረጣችሁ ክፍት ቦታው ላይ አስገቡ።

|  |  |  |  |  |
|---|---|---|---|---|
| ማየት | መቅመስ | መስማት | መዳሰስ | ማሽተት |

በሬዲዮ ስለሎሚ ጥቅም ሲነገር መስማት ቻልኩ። ሰምቼ ለእናቴ "ሎሚ ግዥልኝ" አልኩ። "ተገዝቷል፣ ቦርሳው ውስጥ ፈልገው" አለችኝ። የእናቴን ቦርሳ መዳሰስ ደስ ይለኛል። በጣም ይለሰልሳል። ቦርሳውን እየዳሰስኩ ወደውስጥ ማየት ስሞክር፣ ትንሽ ሎሚ አየሁ። አነሳሁት። ለእናቴ "አፍንጫዬን ሳላስጠጋ ማሽተት እችላለሁ?" ብዬ ጠየቅኳት። "አፍንጫህ ላይ ብዙ ሳታስጠጋ አሽትተው" አለችኝ። ሳሸተው ደስ አለኝ። "ቆርጠሽ ስጭኝና ልምጠጠው" አልኳት። ቆርጣ ሰጠችኝ። ከመምጠጤ በፊት በምላሴ መቅመስ ፈለግኩ። ቀመስኩት። በጣም ጎመዘዘኝ።


© www.keenworksheets.com